**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ**

**የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት**

**ዩኒቨርሲቲው** የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት **የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ** ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ **የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት** ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በማሻሻያ ቁጥር 1146/2011 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታዩ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ፤ የዕርዳታ፤ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ

<u>**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**</u>

**የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ** የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ዩኒቨርሲቲዉ በተለያዩ ጊዜያት ተጋባዥ መምህራንን በመጋበዝ ውል በመግባት የመማር ማስተማር አገልግሎት እያገኘ ሲሆን ለመምህራን ክፍያ ሲፈጽም መንግስት ባስቀመጠዉ የክፍያ ተመን መሠረት ክፍያ መፈጸም ሲገባዉ ከመመሪያ ውጭ ሊከፈል ከሚገባዉ በላይ በድምሩ ብር 251,320.00 ለተጋባዥ መምህራን በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
2. ዩኒቨርሲቲው የICT ኔትወርክ ሥራ (ICT Network Installation) ለማሰራት ከገባው ውል በላይ ብር 53,391.91 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤

3. ለኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ዕውቀት ሽግግር ማህበር ለተፈጸመው የድጋፍ ክፍያ ብር 100,000.00 የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝም ሆነ የባንክ አድቫይስ ያልቀረበ በመሆኑ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
4. በተከታታይ ትምህርት መርሀ-ግብር ቅዳሜና እሁድ (week-end) የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን የተከፈለው ብር **11,209,226.00** ከውስጥ ገቢ ሂሳብ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፤
5. በ2013 በጀት ዓመት ለተፈጸመ ለተማሪዎች መኝታ ቤት የሚውል ሎከር ግዥ ብር 1,287,885.00 ከበጀት ዓመቱ ውጭ በ2014 በጀት ዓመት ተከፍሎ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
6. ለግንባታ ሥራ ብር 119,147.02 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት **የዩኒቨርሲቲው** የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፤ የተፈጸመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. **<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች</u>** <u>(Emphasis of Matters)፤</u>
   1.1. በድምሩ ብር 3,492,365.00 የወጪ ሂሳብ በትክክለኛው ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡
2. **<u>የሕጋዊነት ጉዳዮች</u>** <u>(Compliance Matters)፤</u>
   2.1. የግዢ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብና በግዢ ዕቅድ በመያዝ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት የተለያዩ አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዢው መፈጸም ሲገባው ከመመሪያ ውጭ ያለውድድር በቀጥታ የግዢ ዘዴ የምግብ ግብአት ግዢ ተፈጽሞ ብር 29,383,900.00 የተከፈለ መሆኑ፤
   2.2. በድምሩ ብር 12,292,674.08 ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3. **ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፤**

3.1. የዩኒቨርሲቲው ንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

**በዕቃ ግምጃ ቤት፤**

- አዳዲስ ወንበሮች አገልግሎት ከማይሰጡ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፤

**በዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል ዕቃ ግምጃ ቤት፤**

- ለአላቂና ቋሚ ዕቃዎች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- የተበላሹ (አገልግሎት መስጠት የማይችሉ) የተለያዩ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪነተሮች፣ የፋይል ካቢኔት፣ የፀሐፊ ጠረጴዛ.....ወ.ዘ.ተ) ሳይወገዱ በግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤
- መጠገን የሚችሉና መጠገን የማይችሉ የተበላሹ የታካሚ አልጋዎች ሳይለዩ በአንድ ላይ ተደባልቀው በሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3.2. የዩኒቨርሲቲው የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 እና በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ሁለት ተሽከርካሪዎች (1 ሚትሱቢሽ መኪና የሠሌዳ ቁጥር የሌለው እና 1 ፎርድ ሬንጀር መኪና የሠሌዳ ቁጥር 4-02293 ኦሮ) የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3.3. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

**የ2013 በጀት ዓመት ግኝቶች፤**

- ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ስራ ገበታቸው የሚመለሱበት ጊዜ ያለፈባቸው ትምህርት ላይ መሆን አለመሆናቸው ማረጋገጫ ሳይኖር ትምህርት ላይ እንዳሉ ተደርጎ ለአንድ መምህር የወር ሙሉ ደመወዝ ብር 9,056.00፣ የቤት አበል ብር

800.00 እና የትምህርት ድጎማ 1,350.00 በድምሩ ብር 11,206.00 የስምንት ወር በድምሩ ብር 89,648.00 አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤

- ዩኒቨርሲቲዉ በተለያዩ ጊዜያት ከተጋባዥ መምህራን ጋር ውል በመግባት የመማር ማስተማር አገልግሎት እያገኘ ሲሆን ለመምህራኑ ክፍያ ሲፈጸም ለአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መንግስት ባስቀመጠው ሰዓት ክፍያ መፈጸም ሲገባው ባስተማሩት ክሬዲት ሀወር (credit hour) ላይ 1.5 ከመመሪያ ውጭ በመጨመር መከፈል ከሚገባው በላይ በድምሩ ብር 173,440.00 በብልጫ ክፍያ የፈፀመ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 5,799,901.49 የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 9,083,626.10 መቀነስ የነበረበት የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ያልተቀነሰ እና በወጪም ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- ለተለያዩ የሥራ ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጽም ለተከፈለው ክፍያ በድርጅቶቹ ስም የታተመ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 5,818,801.39 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 21,121,846.28 ለተለያዩ ስራ ተቋራጮች ከተገባው ውል በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 6,370,849.51 ለተለያዩ ስራ ተቋራጮች ከተሰራው ስራ በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ከበጀት ዓመቱ ውጭ ተከፍሎ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤
- በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 712,756.71 መቀነስ የነበረበት የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ ያልተያዘ መሆኑ፤
- በተከታታይ ትምህርት መርሀ ግብር በእረፍት ጊዜያቸው ቅዳሜ እና እሁድ ከፍለው የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው በድምሩ ብር 3,591,220.12 ከመደበኛ በጀት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚፈለግ ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ፤

**የ2012 በጀት ዓመት ግኝቶች፤**

- መምህራን በገቡት ውል መሰረት ትምህርታቸውን አጠናቀው መመለስ ባለባቸው ጊዜ ውስጥ መመለስ ሲገባቸው የመመለሻ ጊዜ ያሳለፉ መምህራን ያቋረጡ ወይም ያራዘሙበትን ምክንያት የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ሳያቀርቡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ስራ ገበታቸው የሚመለሱበት ጊዜ ያለፈባቸው ትምህርት ላይ መሆን አለመሆናቸው ማረጋገጫ ሳይኖር ትምህርት ላይ እንዳሉ ተደርጎ በድምሩ ብር 965,687.00 የተከፈለ መሆኑ፤
- በክረምት እና በእረፍት ቀናት የተከታታይ ትምህርት ላስተማሩ መምህራን በድምሩ ብር 7,927,253.90 ከወስጥ ገቢ ሂሳብ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 5,457,269.20 የወጪ ሂሳብ በተገቢው ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

**መጋቢት 2015**